ሞዓ አንበሳ

'Moa Anbessa'

ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል

The Conquering Lion

Ethiopians For Constitutional Monarchy

ጋዜጣዊ መግለጫ

ወያኔ ከሻብያ ጋር በመወገን በጋራ የኢትዮጵያን መከላከያ ኃይል አፈራርሰው፣ ሠራዊቷ ተበታትኖ ተከላካይ ኃይል አልባ መቅረቷን በማረጋገጥ የአላንዳች ሕዝባዊ ውሳኔ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል አድርገዋል። የጎንደርና የወሎ ጠቅላይ ግዛቶች ለም አውራጃዎችን አምባገነናዊ ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ በትግራይ ጠቅላይ ግዛት ሥር እንዲጠቃለሉ አድረገዋል። አሁን በወያኔ አመቻችነትና በሻብያ ፊትውራሪነት በተከፈተው ጦርነት ሳቢያ ኩታ ገጠም በሆኑት ጠቅላይ ግዛቶች፣ በኤርትራና በትግራይ ጠቅላይ ግዛቶች ሕዝብ ላይ ለደረሰው እልቂትና ለወደመው ንብረት ተጠያቂዎቹ የሻብያ አምባገነን መሪዎች መሆናቸውን የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ያምንበታል። በሕዝብ ላይ የተፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን ጭፍጨፋ አጥብቀን እያወገዝን፣ ጦርነቱ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን። የሻብያ ወራሪ ኃይልም በጉልበት ከያዛቸው የትግራይና የወሎ ጠቅላይ ግዛቶች አውረጃዎች በአስቸኳይ እንዲወጣ እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ የዘውድ ምክር ቤት በዜጋዎች መካከል የሚፈጠር ማናቸውንም ወደ እልቂት የሚያመራ አለመግባባት የማስታረቅና የማስወገድ ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም የኢትዮጵያ የዘውድ ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም በአገራችን ላይ ያንዣበበውን የጥፋት አደጋ ለማስወገድ ወስኗል። ስለዚህ ነፃነት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የጥንት አባቶቹን ፈለግ በመከተል፣ በየአካባቢው በመደራጀት አገሩን ከማናቸውም ወራሪ ኃይል እንዲከላከልና መብቱንም እንዲያስከብር አደራ እንላለን።

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሃበ እግዚአብሔር።

ከዘውድ ምክር ቤት፣ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል
የምሥራቅ አፍሪቃ ማዕከላዊ ጽ/ቤት።
ሐምሌ 5 ቀን 1990 ዓ, ም